# ሞረድ ሲደንዝ በቢለዋ ይሳላል

## (የበዓሉ ግርማ ጉዳይ)

- ሲራክ ዮፍታሄ

ዛሬ የምንገኝበት ዲሞክራሲያዊና ቴክኖሎጂካዊ ዘመን ህዝባዊና መንግስታዊ እውቅና ስለነበረው አንድ ሰው የአሟሟት ምስጢር ጥያቄ ማቅረብ ወንጀል አይደለም። ግርድፍ ማስረጃን አንተርሶ እውነታው እንዲታወቅ መጻፍም አስተዋይ ህሊና ላለው ሰው መጥፎነቱ አይታየውም። ይልቁንም ተጠየቅነቱ ፋይዳ የሚኖረው ለምን የአንድ ሰው አሟሟት ብቻ የሌሎች ወገኖቻችን አሟሟትም ይታወቅ የሚል መሰረታዊ ጥያቄ ከተነሳ ብቻ ነው። ይህም ቢሆን ይቻላል፡፡ እኔ ግን ጥያቄውን ያቀረብኩት በቅርብ ስለማውቀውና ካገኘሁት ማስረጃም ተነስቼ ነው። ሌሎቹ ደግሞ እንውቃለንና ማስረጃም አለን ብለው ቢነሱ መሰረተ ሀሳባቸውን ደጋፊ እንጅ ተቃዋሚ አይደለሁም ቢሉ አጠቃላይ ትኩረቱ ወደ ዋናው **የአቶ በዓሉ ግርማ አሟሟት ተጠየቅነት** ያንደረድረናል።

ለዚህ ጽሑፌ መነሻ ምክንያት የሆነኝ የደራሲ **በዓሉ ግርማን አሟሟት** አስመልክተው ጋዜጠኛና ደራሲ አበራ ለማ ባቀረቡት ጽሑፍ ላይ እየቀረበ ያለው መረን የለቀቀ ስድብና ዉርጅብኝ አስገርሞኝ ነው። በተለይም አቶ **ታሪኩ አባዳማ እና** አቶ **ተስፋዬ ተሰማ** በECADF, በአቡጊዳና ባንዳንድ ድረ ገጾች ላይ የአበራ ለማ ጽሑፍን በመቃወም ጽፈዋል። እንደ ግለሰብ መብታችውን አከብራለሁ። እንደየወል ጉዳይ ደግሞ ተቃውሚቸው ዘለፋና ሰብዕና ተኮር በመሆኑ የአስተማሪነት መልእክት ስለሌለው እቃወማቸዋለሁ።

ደራሲ አበራ ለማ ከልጅነት እስከ ሽበት በሚታወቁበትና በሚጠሩበት በራሳቸው ስም መጻፋቸው እራሱ፣ በራሳቸው የሚተማመኑና ጽሑፋቸውን አስመልክቶም ለሚነሳ ማናቸውም ተችት ወይም ክስ ራሳቸውን ችለው ለመጋፈጥ ዝግጁ መሆናቸውን ከወዲሁ ያሳያል። በአበራ ጽሑፍ ውስጥ ስማቸው የተጠቀሱ ግለሰቦችም እንዲሁ ራሳቸውን ችለው ለመከራከርም ሆነ ለመወያየት ከበቂ በላይ ብቃት ያላችውና ከራሳቸው አልፈው ለሌላው ሊቆሙ እንደሚችሉ ይታወቃል። ታድያ እኛ አንባቢያን ከግራና ከቀኙ የሚወረወሩትን መሰረታዊ ነጥቦች መርምረንና መዝነን ወደ አንድ ብይን ለመምጣት ከመሻት ይልቅ ቀድመንና አንድ ወገንን ደግፈን በስድብ ናዳ መረባረብ " የምጣዱ እያለ የእንቅቡ ተንጣጣ " አይሆንብንም? እዚህ ላይ ሩቅ ሳንሄድ አንተስ ለአበራ ጉዳይ ምን አገባህ ? የሚል ጥያቄ ቢቀርብ መልሴ አጭርና ግልጽ ነው። ይህም የታሪኩ አባዳማ እና የተስፋዬ ተሰማ ምክንያታዊ ያልሆነ ወገንተኝነትና አፈቀላጤነት ነው የሚል ይሆናል። የነእገሌን ስም ለምን ጠቀስክ ብሎ መጠየቅ አግባብነት አለው ቢባል እንኩዋን አንዱን ወገን በመዝለፍና አላግባብ በመፈረጅ የሚቀርብ ገጸ በረከት ግን ውሻ በበላበት ይጮሃል የሚል ትችት ማስነሳቱ አይቀርም። ወጣም ወረደ በአበራ ለማ ጽሑፍ ላይ የተሰጡትን አስተያየቶች አንተርሼ ግላዊ አስተያየቴን አንደሚከተለው አቀርባለሁ።

### *ሀ. የአቶ ታሪኩ አባዳማ አስተያየትና ግላዊ ምልከታዬ*

*** አቶ ታሪኩ ጋዜጠኛ አበራ ባቀረቡት ጽሑፍ ላይ ሁለት የተለያዩ ክፍሎች አስተያየት እንደሰጡና ሁለቱም የሰጡት አስተያየት ስህተት እንደሆነ ይነግሩናል። አያይዘውም ለእነኝህ ስህተቶች መፈጠርም ዋና ተጠያቂው አበራ ነው ይላሉ።ታሪኩ ምን ሊሉን ነው የፈልጉት? አበራ የሚጠየቁት በጽሑፋቸው ነው ወይስ ሌሎቹ የተሳሳተ አስተያየት በመስጠታቸው ነው? ወይስ አበራ ተሳሳቱ አሏቸው ነው የሚሉን? ታሪኩ ዝም ብለው አበራን አላግባብ መቃወም ስለፈለጉ ብቻ ሌሎችንም ያሳሳተ እርሱ ነውና እርሱ ማለት የአጥፊዎች አጥፊ ለማለት እየዳዱ እንደሆነ ዐረፍተ ነገሮችዎ ይናገራሉ። አካሄድዎ "ሊበሏት የፈለጓትን አሞራ ስሟን የሏታል ዥግራ" መሰለኝ ሳጤነው። ሲሰባሰብ ታሪኩ

የሚሉን አበራም ሁለቱ አስተያየት ሰጭዎችም ስህተተኞች ናቸው ነው። ታድያ ማን ነው ትክክል? ሲባሉ "ዘራፍ! ታሪኩ ኣባዳማ ነዋ!..." ሊሉን መሰለኝ። እናንተ ሁለታችሁም ትክክል ኣይደላችሁም ብሎ አስተያየት ለመስጠት መጀመር እኔ የምለው ብቻ ነው ትክክል እመኑኝ ለማለትና ትኩረት ለመሳብ የምታገለግል ቀቢጸ ተስፋዊ አቀራረብ ናት። ይህቺ እኔ ብቻ ያልኩት ይሁን አባዜ የተዋሃደችዎ ቀድሞ ይሰሩበት ወይም ....... ከነበረው የህዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ጽ/ቤት ሳትሆን ኣትቀርም። ችግር ነው ከአብሮ ኣደግ ጋር ኣትሰደድ ይባል የለ ።ታሪኩ አይዞን ለትዝታ ያህልና ትንሽም ላስቅዎ ብዬ እንጅ አንዳንዶቹ አንደሚያስቡት ባለፈ ታሪክዎ ለማስፈራራት አይደለም አባ። ደግሞስ በስደት ዓለም ማን ፈሪ ማን አስፈራሪ ሊሆን ይቻለዋል? እንዳው ታሪክን መዝለል አይቻለምና ነው ማንሳቴ። ይህንን ማንሳቴ ካስቀየመዎ ደግሞ ታላቅ ይቅርታ።

*** በመቀጠልም አቶ አስፋው ዳምጤ **የበዓሉ ግርማ** ከስራ መታገድ ሳያስፈራቸው እቤቱ መመላለሳቸውን የሚጠቅሱት ታሪኩ አባዳማ **በዓሉ** ደብዛው ከጠፋ በኋላ እርሳቸውም አብረው ቢጠፉ አይፈረድባቸውም። ፈርተውም ሊሆን ይችላል ይሉናል። መጽሐፍ ጽፈሃል ተብለው ከስልጣናቸው ከታገዱት ከጓደኛቸው ጋር ሳይፈሩ መለኪያ ሲያነሱና በቤታቸው ሲመላለሱ የነበሩት ሰው ጓደኛቸው ጭራሹኑ ደብዛቸው ሲጠፋ የአፋልጉኝ ጩኸት ማሰማት ሁኔታው ባይፈቅድላቸው እንኳን ወደቤቱ ሂደው ቤተሰቡን መጠየቅ ምን ያስፈራቸዋል ተብሎ ቢጠየቅ መልስ የሚፈለገው ከራሳችው ከኣቶ አስፋው ዳምጤ እንጂ ከታሪኩ አባዳማ ሊሆን አይችልም። በርግጥ በስርዓቱ የነበረ እንደሚያውቀው ሁሉ እንኳን አንድ ትልቅ ባለስልጣን ቀርቶ፣ ተራ ሰው ቢሆንም በመንግስት ሲታፈን ሁሉም እንደሚሸሽ የታወቃል። ሆኖም ግን ቤተሰባችውን ምን ያሸሻል? በባህላችንም የአንድ የቅርብ ጓደኛ ቤተሰብ እንዲህ ባለ ክፉ ቀን ሀዘኑና ፀፀቱ የማይጠፋ፣ አልቅሶ መቅበር እንደጸጋ ሆኖበት ይህን ለተነፈገ ቤተሰብ በቅርብ ማጽናናት ከቅርብ ጓደኛ በጣሙን የሚጠበቅ ነበር። **ከበዓሉ ግርማ** ታፍኖ መጥፋት በኋላ ደረጃው ባይበዛባችውም የኲራዝ አሳታሚ ድርጅት ም/ዋና ሥራ አስኪያጅ ለመሆን የቻሉት አቶ አስፋው ዳምጤ ታሪኩ ሊንግረን እንደሚሞክረው ብዙ አይዳፈሩት እንጅ ብዙም አይፈሩትም። ለምን ቢባል ከዛ በፊትም የደርጉ ቋሚ ተጠሪ ሆነው ለቤተ መንግስቱም ሆነ ለባለስልጣናቱ ባዕድና እንግዳ አልንበሩምና። ስለሆነም ፈርተው ቀሩ አይመስልም። ባህላችንን ሰብረው እንደሸሹ ቀሩ አይዋጥም። እናም ሀቁን ራሳቸው በህይዎት ያሉት ወይም ታሪክ አንድ ቀን ጭብጥ ያለው ማብራሪያ ይሰጠን ይሆናል የደራሲ አበራ ጥያቄም ዝም ኣትበሉ ነውና። **የአሟሟቱን ታሪክ** እንጅ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን **በዓሉን** ካጣነውማ ሦስት ኣሰርቶች ተቆጠሩ እኮ።

*** " **በዓሉን** የበላውማ ደርግ የሚባል ዥብ ነው።" ታሪኩ ኣባዳማ! አሁን አበራ ላቀረቡት የአሟሟት ጥያቄ ይኼ መልስ የሆናል ብለው ነው? "የትኛው ዥብ ነው የበላቸው? ምነው አልጮህ አለ?" እኮ ነው መሰረታዊ የአበራ ጥያቄም። የሚያውቁት ጉዳይ ካለ ኦፐሬሽኑን ያብራሩ ካላወቁ ዝም ብለው ሌሎች የሚያውቁ እስኪያገልጡልን ድረስ ይጠብቁ። እርስዎ እኮ ስለጉዳዩ የሚያውቁ ሰዎች መልስ እንዳይሰጡ ደርግ የሚባል ዥብ ነው የበላው እያሉ በጥቅል መልስዎ ኣገር ባወቀው ፀሐይ በሞቀው እውነታ ያላዝኑብናል።ደርግ እኮ አንድ መቶ ሀያ ያህል አባላት የነበሩት መንግስታዊ አካል ነበር። ታሪኩ በእውነት እልዎታለሁ በዓሉን የበላውማ ደርግ የሚባል ዥብ ነው ብሎ በተራ አገላለጽ ማለፍ ምጻታዊ አገላልጽና በትክክልም በሟቹ ቤተሰብና በኢትዮጵያ ሕዝብ የፍትህ ጥያቄ ላይ ማፌዝ ነው። ከዛም ሲያልፍ **የበዓሉን** ታሪክ አረም በማልበስ ለገዳይና ኣስገዳይ በጨረቃ ጥላ ዘርግቶ ማሽቃበጥ ይሆናል። ከዚህ አድርጎትዎ ጋር አንድ የሚስማማ የአባቶች የአንጋገር ፈሊጥ ትዝ አለኝ **"ስልብ አሽከር በጌታው ብልት ይፎክራል "** የሚለው።

*** መመኘት ወንጀል አይደለም። በጣም የሚመቸኝ ውብ አባባል ነው።ታሪኩ ጥሩ ብለዋልና እኔም እስማማበታለሁ። ስለሆነም ታዋቂው ጋዜጠኛ አቶ ሙሉጌታ ሉሌ ከመምሪያ ኃላፊነት የም/ሚኒስትርነት ደረጃ ቢመኙ ወንጀል ሊባል ኣይችልም። የሰው ልጅ በተፈጥሮው ከፍ እያለና እየተሻሻለ መሄድን እንጅ ወደታች መውረድና ቁልቁል መሄድን አይመኝም። አይመርጥምም። ስለሆነም አባባልዎን ተቀብያለሁ ብልም አንዳንድ ነጥቦችን ግን ማመላከት እፈልጋለሁ። እንደተባለው በማናችውም መልኩ ቢፈተሽ የሰው ልጅና ምኞት ተለያይተው አያውቁም። እንዳውም ፈረንጆቹ

በጥናት እንዳረጋገጡት ከሆነ የሰው ልጅ አንደኛው ፍላጎቱ ሲሟላ ከመቅጽበት ሌላኛው ይተካል ይላሉ። በራሳቸው አባባልም Theory of Need says " When one of your need is satisfied immediately the other replaces. " እንግዲህ መመኘት ከሰው ልጅ ጋር የተሳሰረና ተፈጥሯዊም ይሁን እንጅ በውስብስቡ የህብረተሰብ ክንዋኔ ውስጥ መንፈሳዊ እና እርኩሳዊ ገፅታ ይታይበታል። ለምሳሌ ተምሮ ራስን ትልቅ ቦታ ለማድረስም ሆነ በዕውቀትና በስራ ጎልብቶ እድገትን መመኘት ክፋት የለውምና መንፈሳዊ ምኞት ልንለው እንችላለን። በአንጻሩም በአግድሞሽ መስፈርት ተሸጋግሮ ያለ ብቃትና ያለችሎታ ከደረቅ ፍላጎት ብቻ ተነስቶ ከሁሉም በላይ በሌላው አንጀራና ሕይወት ጣልቃ በመግባትና በአቋርቦሽ ብቻ ደረጃን ለማሳደግ የሚደረግ ሩጫ በአጠቃላይ የአንዱን ሕይወት አበላሽቶ የራስን ምኞት ለማሳካት የሚደረግ ማናቸውም ምኞት እርኩሳዊ ምኞት ከመባል ኣያልፍም። ስለዚህ ኣቶ ታሪኩ እንዳሉት መመኘት በራሱ ጥፋትም ሆነ ወንጀል ሊባል አይችልም። ይህም ስለተባለ አንዳንድ ሰዎች ተሳስተው ከሆነ አጠቃላይ ባህርይ ባለው ምኞት ሽፋን ልንከላከልላቸው ብንሞክር ሌላ ስህተት መስራት ይሆናልና የብይን ሚዛናችንን በጥንቃቄ እንያዘው እላለሁ።

በአጠቃላይ ኣቶ ታሪኩ ኣባዳማ **የደራሲ በዓሉ ግርማን አሟሟት** አስመልከተው አቶ አበራ ለማ ያቀረቡትን ጭብጥ አዘል ጥናታዊ ጽሑፍ ኣሳንሰውና ደረጃውንም ወደ መስርያ ቤት ሽኩቻ ዝቅ አድርገው በአለቃና ምንዝር ቅራኔ ብቻ ወስነውታል። ይህ በፍጹም ስህተት ነው። የብዙሃኑ የውስጥ ሕሊና እሾህ ሆኖ ለሚኖረው ግፋዊ አገዳደል ጥያቄ፣ ለተጎዳ ህሊና እረፍት ሲሉ ጉዳዩን የሚያውቁት እንኳን እንዳይናገሩ መሰረታዊ የሆነውን ጥያቄ ወደ ጎን በማስቀመጥ፣ በኣቶ ሙሉጌታ ሉሌ እና በኣቶ አበራ ለማ አለመጣጣም የተፈጠረ ተራ ጉዳይ አስምስለው ማቅረብዎ ከአንድ ጋዜጠኛ ነበርኩ ከሚለን ባለሙያ ኣይጠበቅም። የሚወዷቸውና የሚያከብሯችው ግለሰቦች ስም ተጠቀሰ ብለው ያቀረቡት ትችታዊ አስተያየት አንኳር ጥያቄው አረም እንዲበላውና ይህም አልቅሶ በመቅበር መጽናናትን ላጡት **ለበዓሉ ግርማ** ቤተሰብ ትልቅ የሞራል ድቀትን ያስከትላል በማለት ባቀረቡት ጽሑፍ ከልብ ማዘኔን ሳልደብቅ ልገልጽልዎት እሻለሁ።

## <u>ለ.የተስፋዬ ተሰማ ትችትና የኔ ምልከታ</u>

******* ሲጀመር ጽሑፋቸው በጣም ድግግሞሽ / redundancy / ስለሚበዛበት በአንድ ቦታ ላይ መነሻ ብለው የሚያቀርቡት ሃሳብ ሌላ ቦታ ላይ ውጤት ሆኖ ይቀርባል። ሌላ ቀርቶ በአንድ ነጠላ አንቀጽ ውስጥ ሲጅምሩ ይገነቡትና ፍጻሜው ላይ ሲደርሱ ደግሞ ያፈርሱታል። ለምሳሌ ይህን አባባላቸውን እንየው...

> " ለዚህ የውሸት ክስ አሁንም ኣስፋው ዳምጤን በቅርቡ ከሚያውቁ ሰው የሰማሁት ወ/ሮ አልማዝ (የበዓሉ ባለቤት ) እና ደራሲ አስፋው ዳምጤ በአቶ **በዓሉ** ጉዳይ ተገናኝተው አውርተዋል። በመሃላቸው የተፈጠረ ቅሬታ አለ። እሱን ደግሞ አስፋው ዳምጤ እንደ አበራ ለማ ስላልሆኑ እውነቱን እንደ ጥላሁን ገሠሠ **ሆድ ይፍጀው** ብለው የሚሉ ይመስለኛል። ህዝብ ይወቀው ብለው የራሳቸውን እውነት ቢያወሩ ጥሩ ነው። " ይላሉ፡፡

ተመልከቱ እንግዴህ ሆድ ይፍጀው ብለው ዝም ማለታችውን መጀመሪያ ላይ አበጁ ይሉና ወረድ ብለው ደግሞ እውነቱን ሕዝብ እንዲያውቀው ቢናገሩ ጥሩ ነው ይሉናል። በዚህ አካሄድ እኮ አቶ አበራ ለማም ያሉት ሆድ ይፍጀው ብላችሁ ዝም አትበሉ የምታውቁ ሰዎች የምታውቁትን ንገሩን ነው። ታድያ ምኑ ላይ ነው ያቶ አበራ ስህተት? የምታውቁ ሰዎች የምታውቁትን ተንፍሱ የሚለው የኣበራ ጥሪ የግድ በጽሕፋቸው ላይ ስማቸውን የጠቀሱትን ግለሰቦች ብቻ አይመለከትም። ጉዳዩ ከቀድሞው የሀገሪቱ መሪ ከኮ/ል መንግስቱ ኃ/ማርያም ጀምሮ በየደረጃው የነበሩትን የፓርቲና የመንግስት ባልሰጣናትን የሁሉ የሚያካትት ነው። ይህን ማለት ደግሞ ውሸታም እብድ ሞኝ አስመሳይ ሴረኛ ..... አስብሎ ዘላንኛ የሚያዘልፍ ምክንያት ጭርሱኑ ሊኖር አይችልም፡፡ በግል ያለ ግላዊ ጥላቻ ካልሆነ በስተቀር የጥያቄው ሁለንተናዊ እውነታ መነሳቱ ከቶም ሊነወር አይገባውም፡፡

*** በአንድ በኩል በዓሉን የመሰለ ታላቅ ሰው እንደ ዋዛ ደብዛው ጠፍቶ መቅረቱ ያሳዘናቸው አቶ ተስፋዬ በሌላ በኩል ደግሞ **ስለበዓሉ አሟሟት** የሚጠይቀውን ጽሑፍ ሲኮንኑ ይታያሉ። ለዚህ እውነታ ራሳቸው በራሳቸው አገላልጽ ያሰፈሩትን ቀጥለን አንመልከት፡፡

> “ **በዓሉ ግርማን** የሚያክል በኢትዮጵያ ጋዜጠኝነትና ስነ ጽሑፍ ታላቅ ቦታ የነበረው ሰው እንደዋዛ ወጥቶ መቅረቱ ወይም ያለ በቂ ምክንያት መገደሉ የሁላችንም ሀዘንና የልብ ስብራት ነው። የዚህን ታላቅ ሰው የአገዳደል ምስጢር ማወቅና ለማወቅ ጥረት ማድረግ መቀጠል ያለበት በመሆኑ ሁሉም ወገን ኃላፊነት እንዳለበት እሙን ነው ። “ ይላሉ ደሞ ለማለት!

አቶ ተስፋዬ ታድያ አበራ ለማ **ስለ በዓሉ ግርማ አሟሟት** ቢጽፉ ለምን የስድብ ውርጅብኝ ያወርዱባቸዋል? ነው ወይስ ጥያቄውን እርስዎና መሰሎችዎ ሲያነሱት ሰብአዊና መንፈስዊ አበራ ሲጠይቁት ግን ከመቅጽበት ግላዊና እርኩሳዊ ይሆናል ሊሉን እየሞከሩ ነው? ይህ አመለካከትዎ ሩቅ አይደለም አንድ ፈርማታ አይስኬድዎምና በበዓሉ ጉዳይ ከአበራ ጋር ሣይሆን ከራስዎ ጋር ቢታገሉና እርቅ ቢፈጥሩ ሸጋ ነው። ደግሞስ በበዓሉ ጉዳይ ምን አለያያችሁ? እርስዎ የሚሉት ( ከልብ ከሆነ! ) የበዓሉ ጉዳይ የሁላችንም ስለሆነ አገዳደሉን ለማወቅ ጥረት ማድረግ አለብን ነው፡፡ እግዜብሔር ይባርክዎ ። አበራም ያሉት **በዓሉን** የበሉ ዥቦች ምነው አልጮህ አሉ? ነው እግዚኣብሔር ይባርካቸው። ታድያ አበራ ለማንና ተስፋዬ ተሰማን ምን ያለያያቸዋል? **የበዓሉ አሟሟት የይታወቅ ጥያቄ** ? NO. NO. NO. ምናልባት የግል ጥላቻ? የማውቀው ጉዳይ የለም። ግን ከጤነኛ አእምሮ ለመመንጨቱ እጠራጠራለሁ፡፡

እንዳውም አቶ ተስፋዬ ቀጠል ያደርጉና ”........በዚህ ቅኝት የተጻፉ ጽሑፎች በህዝቡ ውስጥ ሲሰራጩ **የበዓሉን አሟሟት ምስጢር** የበለጠ ውሉን እያጠፋውና እያወሳሰበው ይመጣል የሚል ስጋት አለኝ” ይላሉ። የአበራ ጽሑፍ እኮ ግልጽና በየትኛውም ደረጃ ያለ ሰው አንብቦ በሚረዳው መደበኛ ያማርኛ ቋንቋ የቀረበ ነው፡፡ እንደርሶ ያለ የተምታታበት ሰው በራሱ የተምታታበት ካልሆነ በስተቀር ማንንም አያምታታም። እርስዎም አኮ ተርድተውና ገብቶዎት “ የ**በዓሉ** ጉዳይ የሁላችንም ነው! “ ብለው ብይንዎን አስፍረዋል። አይዞን አይፍሩ **በበዓሉ** ጉዳይ ደንታ የለውም የሚለዎ የለም። ደግሞስ ሰው ያሻውን ቢል ማንነትዎን አይለውጠው፣ ጠንከር ነው እንደ በረሀ፝ኙ ሲጋር ግመሊቱ!!!!

### *** ወንጀልና ወንጀለኛነት

“ ከወንጀሎች ሁሉ ወንጀል ወንጀለኛ ያልሆነን ሰው ወንጀለኛ ማለት ነው“ በጣም የሚመቸኝ የኣቶ ተስፋዬ አባባል ነው። እኔ እንደገባኝ ከሆነ አበራ በግልጽነት ያሰፈሩት ገዥ ሀሳብ ውንጀላ አይደለም። የበዓሉ አሟሟት እስከ መቼ ምስጢራዊ ሆኖ ይደበቃል? እባካችሁ የበላችሁትም ሆነ ሲበሉት ያያችሁ ድምጽችሁን አሰሙን ሌላ ቢቀር ንስሐ ግቡ አይነት ይመስለኛል። ደራሲ አበራ ከተለያዩ ምንጮች ያገኟቸውን ማስረጃዎች እየጠቀሰ፣ የሚመለከታቸውን ሁሉ ያለው መልስ ስጡ እንጂ አቃቤ ሕግ ሆኖ ልፋረዳችሁ አይደለም፡፡ በመሆኑም እገሌ እና እገሌ በበዓሉ አሟሟት ወንጀለኞች ናቸው የሚል አንድም ገላጭ ጭብጥ የለም። ያለማስረጃ በሃሰት ግለሰቦችን ወንጀለው ጽፈው ከሆነ ተወንጃዮቹ በህግ የመከሰስ፣ ወንጃዩም በህግ የመከሰስ መብትና ገዴታ አለባቸው። ደግሞስ **“አንድ ሰው ወንጀለኛነቱ በህጋዊ የፈርድ አካል እስካልተረጋገጠ ድረስ በህግ ፊት ወንጀለኛ አይሆንም“** የሚለውን ሁለንተና ድንጋጌስ አቶ ተስፋዬ ሳይውቁት ቀርተው ነው ወይስ የኣዞ እንባዎ እየፈሰሰ ኣስቸገረዎት ? ከዚህ የወንጀለኛ ፍረጃዎ ሳንወጣ በራስዎ ጽሑፍ ራስዎንም ወንጀለኛ አድርገው ያቀረቡበትን አገላለጽ ላስታውስዎ እፈልጋለሁ ከይቅርታ ጋር - “የበዓሉ ግርማ አሟሟት ጉዳይ የሁላችንም ነው” ካሉ በኋላ ይህን ይሽሩና መልሰው “የበዓሉን ስም እየጠቀሱ የበዓሉ ጠበቃ ነኝ ማለት በአዓሉን እንደገና የመግደል ያክላል” ይላሉ። እንግዲህ አርስዎም የበዓሉን ስም ጠቅሰዋልና ወንጀለኛ ነዎት ብለን በመፈረጅ አለም አቀፍ ፍርድ ቤት እናቅርብዎ ?... ኧረ አየተስተዋለ !

***** የጽሑፍ ደረጃ አመዳደብዎና የሙያ ብቃትዎ**

"… አቶ አበራ ያቀረቡት በእውነተኛ መረጃ ድርቅ የተመታ በመሆኑ እንደ አጭር ልብ ወለድ መለካቱ የተሻለ ሆኖ አግኝቼዋለሁ። የሚያሳዝነው ነገር ጽሑፉ አንደ ልብ ወልድ ቢወሰድ እንኳን ደካማ ከሚባሉት የልብ ወለድ ጽሑፎች የሚመደብ ነው" ይላሉ። እንዴት ያለ ደረጃ ምደባ እንደሆነ አልገባኝም'፡፡ መጀመሪያ አንድን ስነ ጽሑፍ አጭር ልብ ወለድ፣ ረጅም ልብ ወለድ ብሎ ለመፈረጅም ሆነ ይዘቱን መርምሮ ደረጃ ለመስጠት የፍላጎት ሳይሆን የሙያ ባለቤትነትን ብቃት ይጠይቃል። ጠንካራና ደካማ ስነ ጽሑፍን ለመመዘን የሚያገለግሉ ቁልፍ መፍቻዎችን / key devices / ማወቅ በጣሙን ያስፈልጋል። ይህ የስሜት ሳይሆን የሙያ ጉዳይ ነው። በስሜት ተንስተውማ ጋዜጠኛና ደራሲ አበራን አንዴ የቀይ ሽብር ተከሳሽ ሌላ ጊዜ ደግሞ የኢህአዲግ ቀላጤ አድረገው ስለዋቸዋል። ችግሩ እርስዎ እራስዎ ካዲስ አበባ ፎርጅድ አሰርተው አምጥተው በኢትዮሚዲያ ፎረም አማካኝነት ካስበተኑት አሉባልታ ባሻገር ያየነው የለም፡፡ የምስራቁ ድል በሰሜኑም ይደገማል በሚለው የያኔው መርህ መሰረት ብሔራዊ አንድነትን ለማስከበር የዘመተ ዘማች ጋዜጠኛን፣ ተስፋዬ እንደሚሉት ደግሞ በቀይ ሽብር ተዋናይ የሆነን፣ ባለፈው መንግስት ደራሲና የፕሮፖጋንዳ ሠራተኛ ሆኖ ያገለገልን ሰው ወዘተ… በምን መስፈርት ነው የኢህአዲግ ቀንደኛ ተሚጋች ተብሎ የሚፈረጀው? መልሱ አንድ ነው - በስሜት ፈራጆች ዘንድ - ጠለሸት መቀባት!!

ውድ አንባቢዎች ! አቶ ተስፋዬ አቶ አበራን በቀይ ሽብር እንዴት ሊመድቧቸው ቻሉ? የሚለው ጥያቄ ምላሽና ትክክለኛ ታሪኩን ማውቅ ያስፈልጋል። እኔም ጉዳዩን እንዲህ ነው የተረዳሁት ሁለቱም ግልሰቦች ማለት ወንጃይና ተወንጃይ በየፊናቸው ያወጧቸውን ማስረጃ ከተመለከትኩ በኋላ ነው። ደንቆሮ የሰማ ዕለት ያብዳል ይባል የለ! ጭብጡ አንዲህ ነው....

አቶ ተስፋዬ አቶ አበራን በቀይ ሽብር ለመወንጀል ስለፈለጉ ጠቅላይ አቃቢ ህግ የሚገኝ ባለ 46 የተከሳሽ ተጠርጣሪዎች ስም ዝርዝር ያለበት ሰነድ አፈላልገው ያገኛሉ። በዚህ ዝርዝር 27ኛ ላይ "አበራ በሪሁ" የሚባል ተከሳሽ ተጠቅሷል። "አቶ ተስፋዬ" በመደለዝና ኮፒ ኤንድ ፔስት የሚባለውን ቴክኒክ በመጠቀም ".... በሪሁ" በሚለው ያባት ስም ምትክ "… ለማ" የሚለውን ተክተው፤ ኖርዌይ፣ አምስተርዳምና ቤልጂየም ወዘተ… ለሚገኙ ወዳጆቻቸው ይበትናሉ፡፡ በእዚሁ የክስ ፋይል ሌሎች ገጾች ላይም " አበራ በልሁ" እና "አበራ በሪዮ" ተብሎ የተጠቀሰን የተከሳሽ ያባት ስም "በልሁ"ን በ"… ለማ" በመተካት አብረው አያይዘው ይልካሉ፡፡ "አቶ ተስፋዬ" እነዚህን ፎርጅድ ሰነዶች ያደረሷቸው ወዳጆቻቸው እውነተኛ መስሏቸው ካንዱ ወዳንዱ ሲቀባበሉ፣ አንዱ ሀቀኛ ሰው ላቶ አበራ ፎርጅዱን ሰነድ በማቀበል እራስክን ጠብቅ ያላል፡፡ ልብ በሉ ይህን ያዩት ደራሲ አበራ ለማ ደግሞ አርፈው ከተቀመጡበት የስደት ሕይወታቸው ተነስተው፣ "ይህን ቅሌታም በሃቅና በማስረጃ ማንበርከክ አለብኝ!…" ብለው ወደ አዲስ አበባ ለመጀመሪያ ጊዜ በረው የሄዱና "አቶ ተስፋዬ" አዘጋጅተው የበተኑትን ፎርጅድ ሰነድ ለጠቅላይ አቃቢ ህግ አቅርበው ጉዳዩ እንዲጣራላቸው ይጠይቃሉ፡፡ ጠቅላይ አቃቤ ሕግም ጥቄያቸውን ተቀብሎ ፎርጅዱን ከዋናው ሰነድ ጋር ሲያስተያየው ጭርሱን የማይገናኙ መሆናቸውን ላቶ አበራ ይገልጽላቸዋል፡፡ አቶ አበራም የዋናው ሰነድ ትክክለኛ ቅጂ እንዲሰጣቸው በጠየቁት መሰረት፣ ጠቅላይ አቃቤ ሕግ ኮፒ አድርጎና ማህተም መቶ የሰጣቸውን ኦሪጅናል ሰነድ ይዘው ወደ ኖርዌይ ይመለሱና ለወዳጆቻቸው ሁሉ እንዲያውቁት ያሰራጩታል፡፡


"አቶ ተስፋዬ"ም በድርጊታቸው አፍረውና ተሸማቀው አንገታቸውን ደፍተው ከዚያ ወዲህ ድምጻቸው ሳይሰማ ኖረዋል፡፡ ሰሞኑን ግን የበዓሉ ግርማን ጉዳይ ለማዳፈንና የደራሲ አበራን እውነት የማውጣት ጥረት ለማምከን ሲሉ ዳግም ይህን ያጭበረበሩበትን ሰነድ እየጠቃቀሱ ጉሮ ወሸባዬ ሲሉ ተስተውለዋል፡፡ "የሌባ ዓይነ ደረቅ መልሶ ልብ ያደርቅ" እንደሚባለው፣ አቶ ተስፋዬ ነጻነታቸውንና እውነትን ፍለጋ ወደ አገር ቤት የተጓዙትን አቶ አበራን "አገር ቤት ተመላላሽ ወያኔ ሆኗል" ይሉናል፡፡ እውን አቶ ተስፋዬ እርስዎና ቤተሰብዎ አገርዎ ደርሰው ሲመለሱ " ወያኔ ሆኑ" ቢባሉ ፍትሃዊ ነው ይላሉ? ኢትዮጵያ የሚመላለሰውና የሚኖረው ሁሉ "ወያኔ" ከተባለ ታዲያ ምን ተረፈን? ወያኔን ባልተጠረበ ፕሮፓጋንዳዎ በጣም በጣም እየረዱት እንዳለ ያስተዋሉት አልመሰለኝም፡፡ አቶ አበራ

ነጻነታቸውን ለማረጋገጥና በሕዝብ ፊት ሳይሸማቀቁ ለመቆም በራስ ተማምነው እንኳን አገራቸው የትስ ቢሄዱ በምን መመዘኛ ነው የሚነቀፉት? አይ "አቶ ተስፋዬ" ይህን ስምዎን በእውነተኛ ስምዎ በመምሬ አብደላ ቢቀይሩት ያሻል ነበር፡፡ እሺ ይዋሹ ላንዴ - ለዘለኣለሙ ግን ሕሊናን ዋሽቶ መኖር እንዴት ይቻላል? እኔም በቅርቡ አንድ ሰው በፌስቡክ ላይ ከለቀቀው ማሳሰቢያ ይህንን የፎርጅዱንና የኦሪጂናል ሰነዱን ምንና ምንነት ከነማብራሪያው ለመረዳት በመቻሌ በ"አቶ ተስፋዬ" አሳፋሪ ተግባር በጣሙን አፍሬያለሁ ፡፡ ላንባቢዎቼም ለማካፈል ፈቅጃለሁ፡፡

ስለዚህ "አቶ ተስፋዬ"ን መሰል በሬ ወለደ ባዮች ይሁን ብለው ሌላውን እንዳያሳስቱ ትምህርት ይሆን ዘንድ ቀጥሎ ሰነዶቹን በቅደም ተከተል አስቀምጫቸዋለሁ፡፡ በዚህም ውድ አንባቢዎቼ እውነተኛ ፍርዳችሁን ትሰጡ ዘንድ እጠይቃለሁ፡፡

## 1. በ"አቶ ተስፋዬ" የተሰናዳው ፎረጅድ 1ኛ

2. በ"አቶ ተስፋዬ" የተሰናዳው ፎረጅድ 2ኛ



1. ጠቅላይ አቃቤ ሕግ ላቶ አበራ ለማ ማረጋገጫ የሰጠው ኦሪጂናል ቅጂ ፲ኛ

የወ/ወ/ቁ. 630/89

ሚያ 11ት 04/94

ጎኛዎቹ:_ ወንድገን አምበ

ኑረ ሰይድ

ተወሰገን ገ/ሥላሴ

ለቀ ዐቃቢ ሕግ ወ/ሮ ወይንሸት ከበደ

ተከሣሾቹ 1. አርገጤ ወልበው ቀረበ

2. 10 አለቃ ተሻሆን ከበደ ቀረበ

3. በዓነህ ወዲት

4. ደጀኔ ነምጠው ቀረበ

5. ፈቃደ ገብረ ዓብገበ

6. ቢበዳ ለክሣ ይ

7. ዎሳ ወለሌ

8. ወንገቱ ጎጋቶ ዎታለ

9. ሙሉጌታ አወገኘ ቀረበ

10. ኤሊያስ አበፋው ቀረበ

11. ወኪሪያ ወልደሥላሴ

12. ፀጋዬ ደተሻረከ ይ

13. ይወር/ የአብቱ በዎ ያለተወቀ/ከስ ተፈርዷል

14. አዋናፋ ማዎ ቀረበ

15. ሰይድ ልደብ ቀረበ

16. ዋልድርቀ ደማዎ በሌለቸበት

17. ካሙሌስ ወንገሽ ዎታለ

18. ካሙሌስ ወለደ ሚካኤል ዎታለ

19. በቀለ ገብረ ሚካኤል /ሞዎሲ/ ቀረበ

20. ሰለቁ ገበ ቀረበ

21. 10አለቃ አባተ ጀማነህ ዎታለ

22. ኃይሌ ገ/ሥላሴ ቀረበ

23. አሸቱ ማርቆ ዎታለ

24. አፈርሳ አያና ቀረበ

25. ሠረፀ ተሻ በሌለበት

26. ፋጠመ ደገፈ ቀረበ

27. አበራ በሬሣ ቀረበ

28. ፀጋዬ ገዛው በሌለበት

29. ጌታቸው ወባሌ በሌለበት

30. ጠወለስ ገበሬ በሌለበት

31. 10 አለቃ ገዛው አበበ ዎታለ

32. አበማረ ፈገኔ ቀረበ

33. አማረ ሰሳይ ቀረበ

34. ዘካሪዎ ከስ ተፈርዷል

35. አስከገደር ገ/ወደገ በሌለበት

36. ደረጀ ከስ ተፈርዷል

37፣ ፀሐይ ከስ ተፈርዷል

38. ታምራት አበሌሉ ቀረበ

39. አደፍርስ ገቀገቴ ቀረበ

40. ወክገገ ጫኔት ቀረበ

41. ማዎ አበበ ቀረበ

42. ታቀ ሙሉዓለም ቀረበ

43. ወገደወሰገ ደካለኘ በሌለበት

44. ጌታነህ ደበታ ቀረበ

45. ሁሴን አሀመድ በሌለበት

46. በዙነህ ደነቀ ቀረበ

./...

## 2. ጠቅላይ አቃቤ ሕግ ላቶ አበራ ለማ ማረጋገጫ የሰጠው ኦሪጂናል ቅጂ 2ኛ

- 15 -

ሰነድ 1 በአቶ ለማ ሚያዝያ 09/70 ዓ.ም በቁጥር 08/2956/70 የጻፈው ነው በጽሑፍ ደብዳቤ ገለጻቸው የገለጹት ፋሽስት ኢህአፓ የገደሉ አባል ሆነው ቀይሽብር የተካሄደበት ወቅቶች ሰዎ እንዲገለጹ በተጠየቀው መሠረት ቅድ ከተማ ሰላም አቋሟን መስፍን ሰንዶ የተጻፉት ቀይሽብር በአ/1 ቀ. 08 ከለሰ የተካሄደበት ወቅት ተገለጸ የአ/1 አመለካ ፡

2. ሊቀመንበር በበኩሉ እነዚህ ሰዎች የነደፍ የኢህአፓ አባል በመሆናቸው በአ/1 ቀ. 08 በኩል የተወሰ መሆኑን ለደርግ ምርመራ ክፍለ የገለጸበት በ17/8/70 ዓ.ም የጻፈው ደብዳቤ በማስረጃነት ቀርቧል ፡፡

3. በገኛ ዋርጊት 3ኛ የሰነድ ማስረጃ ስለ5ኛ ተከሣሽ ቀርቧል በገኛ ዋርጊት ስለ2ኛ ተከሣሽ የቀረበው 7ኛ የሰነድ ማስረጃ ስለ6ኛ ተከሣሽ የቀረበው 12ኛ የሰነድ ማስረጃ እና ስለ7ኛ ተከሣሽ የተቀረበው 13ኛ የሰነድ ማስረጃ ቀርበዋል

4. ስለ1ኛ ተከሣሽ በገኛ ዋርጊት የተቀመጡት 4ኛ 5ኛ 8ኛ 9ኛ 10ኛ የሰነድ ማስረጃዎች ቀርበዋል

5. አበራ በሰኔ 27ኛ ተከሣሽ ነሐሴ 11/73 ዓ.ም የጻፈው እና የተጠቀሰውን ሙግቱን ለማስመለስ የአ/1 ምሬ አስፈጻሚ ኮሚቴን የጠየቀበት ደብዳቤ ቀርቧል በዚህም ከ1966 ዓ.ም ጀምሮ ለአብዮቱ መታገሉን በቀይሽብርም ጊዜ ገበገበ ሲያደርግ የነበረ መሆኑን የገለጸበት ይገኛል ፡፡

6ኛ ተከሣሽ በአቶ ለማ በገኛ ዘራ የተመለከተው ሰነድ አንድ የሚያስገኝ አይደለም ስለፈረደበት ስለዚህ ውሳኔ ይሰጥበት በሉ ተከራከረ ፣ እኛም ማስረጃዎቹንና ክርክሩን አገናዝበን መርምረናል ፡፡

ዓቃቤ ከመገደላቸው በፊት ሙሉ የተባለችው ዓቃ ርገጤ መዝገቦች በአቶ ለማ በቀለ ገበሬ ማኅበር /ቀምበ/ የገባሉት ኢህአፓ ነበ ብለው ጎኅር 14/70 ዓ.ም የወሰዷት መሆኑ 10 አለቃ አባተ ጀማነህ በከማ ለጋቢ ፈለቀ ገበየሁ የተባሉት ደግሞ ሰለሞን አለሙን በዚሁ ዕለት ሌሊት ከመኖሪያ ቤቱ ከተወሰዱ አስነስተው መውሰዳቸውና በአቶ ለማ እንዲሁ መስፍን ሰለሞን በተመሳሳይ ጊዜ ከመኖሪያቸው አስነስተ ኢህአፓነሀ ብሉ መውሰዱ ተመስክሮአል እነዚህ ሰዎች ሟቾችን ወስዶ በዚህ አይነት ከበላቸው ኢህአፓ ናቸሁ ብለው ከወሰዱዋቸው በኋላ የወሰዳቸው ሀይ ከ/1 ቀ. 08 ነው ምስክሮቹም ከምስክሮቹ አገኙ ከሦስቱ ሟቾች በኋላ ተጠይዞ እዚሁ ቀበሌ በተወሰደ ጊዜ እነዚህን ሟቾች እዚያው ተይዞ አገኛቸዋለሁ ይህ የሆነው በዚያው በተመሳሳይ ሌሊት ነው ይሆን ምስክር በተመሳሳይ ሁኔታ ይዞው ወደቀበሌው የወሰዱት ደግሞ ዮሴፍ ወለሌ እፈርሳ አያና አሸቱ ሚርቆ በቀለ ገበሬ ማኅበር/ቀምበ/ ናቸው ይህ ምስክር እንዳስረዳው በመኪናው የተጫኑት ሟቾች አቶ ወለሌ እና አፈርሳ አያና ከሰዷቸው ይዘው ሄዱ መሆኑን ነገረውታል ፡፡

## 3. ጠቅላይ አቃቤ ሕግ ላቶ አበራ ለማ ማረጋገጫ የሰጠው ኦሪጂናል ቅጂ 3ኛ



፱ 55 ፱

66ኛ ተከሳሽ ሣህለማሪያም ዘለለው

በጽር ጊት አሥራ አምስት እና አሥራ ስድስት

76ኛ እና 68ኛ ተከሳሾች ምናሴ ዘርጋው እና ኡርጋ ሙሉወይ

በጽር ጊት አሥራ አምስት

69ኛ ተከሳሽ ለገሰ ለመንጉ

በጽር ጊት አሥራ ስድስት

70ኛ፣ 71ኛ 72ኛ ተከሳሾች አንዳርጌ ወንበርጊ ከፍሌ ወንበር አበር አለቃ ሙሉነት ወልደሚካኤል

በጽር ጊት አሥራ አምስት

76ኛ ተከሳሽ ገብሬ ቶሌ

በጽር ጊት አሥራ ስድስት

80ኛ ተከሳሽ አበራ በለሁ በጽር ጊት አሥራ ሰምንት

ውስጥ ስንደ ተመለከተው በፖለቲካ ተሥሥራቸው አገሬ የሆነትን ሰዎች ለማጥፋት በማሰብና በመፈለግ የዚህ አይነት ተሰበር አሏቸው በማለት የአህአፖ አባላት ናቸው በማለት ከዚህ በላይ በየስማቸው ትይዩ በየተመለከተ ድርጊቶች ውስጥ የተጠቀሱት ተከሳሾች በተለያየ አይነት የተሳተፉ ደረጃ እንዲገደሉ በማድረጋቸው ግብረአበር መሆናቸው ስለተረጋገጠ በነዚህ በየስማቸው አንፃር የተጠቀሱት ድርጊቶች በመፈፀም በወ/መ/ህ/ቁ281/ሀ/ሥር የተመለከተውን ወንጀል ከአባሪነትና በግብረአበርነት እንዲፈፀም ማድረጋቸው የተረጋገጠ ሆኗል። ስለዚህ በነዚህ ድርጊቶች ሥር ፍ/ቤቱ በነገራችን ቅድም በገለፀው መሠረት እነዚህ ተከሳሾች ተመሳሳይ ማስረጃቸውን ሊያቀርቡ ይገባል ብለናል።

በሌላ በኩል ተከሳሾች

| | |
|---|---|
| 10ኛ አለያስ አበፋው | 50ኛ ከፍያለው ለማ |
| 15ኛ ሠይድ ወይበ | 52ኛ አደም ጀሶ |
| 16ኛ ዘሚወርቅ ይማም | 53ኛ ፍቅሬ ወልደ ጊዮርጊስ |
| 22ኛ ኃይሌ ገብረሥላሴ | 57ኛ በዳ ሊጋሌ |
| 26ኛ ተሾመ ደገፋ | 58ኛ ወ/ር ጫርጤሰ ቦበቃ |
| 27ኛ አበራ በሬቻ | 59ኛ ትዕዛዙ ተከፋማሪያም |
| 29ኛ ጌታቸው ወለሉ | 60ኛ ወንድይፍራው አስማረ |
| 32ኛ አስማረ ፈንታ | 64ኛ ደደ ኪነፄለማሪያም |
| 33ኛ አማረ ሰብይ | 73ኛ ወከንን ዘርጋው |
| 44ኛ ጌታነህ ደበታ | 74ኛ ገ/ሰ ጋሪምባ ዱሬቦ |

ስለትክክለኛ ግልባጭ 55./

## ማጠቃለያ

ደራሲ **በዓሉ ግርማ** በፈጠራ ክሂላቸው ለሀገራችን የስነ-ጽሑፍ ዕድገት ከፍተኛ አስተዋጾ በማድረጋቸው በዘርፉ ብሔራዊ እውቅናንና ክብርን ካገኙ አንቱ የተባሉ ደራስያን አንዱ ናቸው። በነበራቸው መንግስታዊ ስልጣንም አገራቸውንና ህዝባቸውን በቅን በማገልገላቸው የህዝብ ፍቅር ነበራቸው። ምንጊዜም ቢሆን ያመኑበትን ጉዳይ ከማድረግ አንዳችም ቁጥብነት ያልነበራቸው **በዓሉ ግርማ** የሀገራችንንና የቱባ ቱባ ባለስልጣናቱን ጉድፍ ቁልጭ አድርጎ የሚያሳየው መጽሀፋቸው "ኦሮማይ" ለደብዛቸው መጥፍትና በግፍ ለመገደላቸው ዋና ምክንያት እንድሆን በድፍን ኢትዮጵያ ይታወቃል። በዓሉ በግፍ ታፍነው በድኑ አካላቸው ከምድር በታች ቢሆንም ለኢትዮጵያውያን ግን በአዓሉ ምንም ጊዜም በህይወት አሉ፣ ይኖራሉ። እጅግ በተመረጡ ቃላት ታጅበው ልብን በመስቀል የማይረሱቱ ድንቅዬ መጻሕፍቶቻቸው ምን ጊዜም ቢሆን የአሟሟት ታሪካቸውን ሁሌም እንድንጠይቅ ያነሳሱናል። ይህ ሁሌም የህዝብ ጥያቄ የሆነውን የደራሲ በአዓሉ ግርማን የአሟሟት ታሪክ የማወቅ ጥያቄ

አስመልክተው ጋዜጠኛ አበራ ለማ አንድ ጽሁፍ ስለዘከሩን ግላዊ ምስጋናዬ ይድረስዎ። ይህን ጽሁፍ አስመልክተው አንዳንዶቹ የሰጡትን አስተያየት ግላዊ ፍተሻ በማድረግ በሚከተሉት ነጥቦች አስተያዬቴን እቋጫለሁ።

1. በአቶ አበራ ጽሑፍ ላይ ስማቸው የተጠቀሱት አቶ ሙሉጌታ ሉሌ እና አቶ አስፋው ዳምጤ ሁለቱም የዕድሜ ባለፀጋ ብቻ ሳይሆኑ በሙያም የበለጸጉና ሀገራቸውንም በሙያቸው ያገለገሉ አንጋፋ ሰዎች ናቸው። ከሁሉም በላይ ደግሞ ለሚቀርብባቸው ማናቸውም ጉዳይ ራሳቸውን ችለው መቆም ስለሚችሉ 3ኛ ወገን አዛኝና ተቆርቋሪ መስሎ በአቶ አበራ ላይ ያለና የቆየ የግል ቂምን ለመወጣት መሞከር ኢ ሞራላዊ ስለሆነ ሊታረም ይገባል አላለሁ።

2. ደራሲ አበራ ለማ ማንነቱን ሸሽጎና የብዕር ስም ተጠቅሞ የሚፈልገውን አስተያየት መጻፍ ይችል ነበር። ይህን ያልመረጠበት ግን አንድ ሀቅን ይገልጻል። ይህም አግባብ ያለው ትችም ከመጣ ይምጣ እንደ አመጣጡ እኔው ለጻፍኩት እኔው ነኝ ኃላፊው ብሎና ደፍሮ ነው። ይህ የአበራ ጽሑፍ እንዳለ በሌላ ስም ተጽፎ ቢሆን ኖሮ ታሪኩ አባዳማም ሆኑ ተስፋዬ ተሰማና ሌሎች ካቶ አበራ ጽሑፍ ጋር ምንም ዝምድና የሌለው እሪ በከንቱ ጽሁፍ የጻፋችሁ ሁሉ፣ መልስ ከመስጠት ትቆጠቡ ነበር የሚል ግምት አለኝ፡፡ የናንተ ድንበር ዘለል ወገንተኛነት ብዙ ሰዎችን እንዳሳዘነ ከኔ አይነቱ ምላሽ የምትረዱት ይመስለኛል፡፡

3. አንድ አንድ ድህረ ገጾችም የአበራን የውይይት መነሻ ጽሑፍ ሳያወጡ ነገር ግን ፈጥነው የተሰጡ ምላሾችን ማውጣታቸው ትዝብት ላይ ጥሏቸዋል። በአናቱም አንባቢዎች ቅደም ተከተል ያለው እሰጥ እገባን በሚገባ ተከታትለው ወደ ትክክለኛ ብይን እንዳይንደረደሩ ትዕዕኖ አሳድሯል፡፡ ህዝብ ትክክለኛ መረጃ የማግኘት መብት አለው የሚለውን መሰረታዊ አባባልም መሸርሸር ይሆናልና ለወደፊቱ ብርቱ ጥንቃቄ ይደረግ በማለት አንባቢዎቼን እሰናበታለሁ።

sirakyoftahe@gmail.com